גודל- 39x29 ס"מ, ע"ג ניר דופלקס לבן 250 גרם

# ደንቦች
# ወሲባዊ ትንኰሳን ለመከላከል የወጡ ደንቦች

በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ
የሴቶች ቦታን ማስቀደሚያ ባለሥልጣን
www.women.gov.il

በ1998 ዓ.ም. የተደነገገው ወሲባዊ ትንኰሳን የመከላከል ደንብ የሚከተለውን ይመስላል።

**ወሲባዊ ትንኰሳ በሕግ የተከለከለ ድርጊት ነው – ይህ ሕግ ማናቸውንም ዓይነት ወሲባዊ ትንኰሳዎችን ይከለክላል። ወሲባዊ ትንኰሳ ሲፈጽም የተገኘ ሰው እስከ 2 ዓመት የሚደርስ እስራት ሊፈረድበት ይችላል።**

**የተከለከሉ ድርጊቶች፡ ወሲብ** – ነክ ጉዳይ ለመፈጸም ፈልጎ ማስፈራራት፣ በበላይና በበታች ሠራተኛ መካከል ያለውን ግንኙነት ለወሲባዊ ጉዳይ መጠቀሚያ ማድረግ፣ የተወገዘ ድርጊት (አንድ ድርጊት ብቻ ይበቃል)፣ ወሲባዊ መልክ ያላቸው ተደጋጋሚ ጥያቄዎች፣ ስለግለሰብ ወሲባዊነት ተደጋጋሚ አስተያየት መስጠት፣ ስለሰው ወሲባዊ ድርጊት ወይም ዝንባሌው የሚያዋርድ አስተያየት መስጠት (አንድ ድርጊት ብቻ ይበቃል) **የወሲባዊ ትንኰሳ ምሳሌዎች፡** አሠሪ ወም ሠራተኛ የሥራ አጋሩን ወደወሲብ ስሜት መገፋፋት፣ ሰው ማየት የማይገባውን የሰውነት ክፍሉን ያለእሷ ፈቃደኝነት ገልጦ ማሳየት፣ አሠሪ ወይንም ሠራተኛ የሥራ ባልደረባውን "የግብረ ሥጋ ግንኙነት ካላደረግሽ ወይም ከኔ ጋር ካልተዝናናሽ ከሥራ አባርርሻለሁ" ብሎ በግልጽ ወይም ተዘዋዋሪ በሆነ መንገድ የሚያስፈራራ ከሆነ

**ወሲባዊ ትንኰሳ ተብለው የማይታሰቡ ድርጊቶች የትኞቹ ናቸው?** በጋራ ስምምነት፣ በጥሩ መንፈስና በነጻነት የሚደረግ መፈቃቀድ ትንኰሳ ተደርጐ አይታሰብም።

**የተከለከሉ ሴራዎች** – በማንኛውም ሠራተኛ ወይንም ሥራ ፈላጊ ላይ የሚከሰቱ ወሲባዊ ትንኰሳዎች ወይንም የወሲብ ትንኰሳ ክስ ለመሠረተ ሰው ምስክር ሆኖ የቀረበን ሰው መተናኰል/መጉዳት። የዚህ ዓይነት ሴረኛ እስከ 3 ዓመት በእስራት ሊቀጣ ይችላል።

**አለመስማማት** – ወሲባዊ ትንኰሳ የሚፈጸምበት ሰው በግልጽ ፍቃደኛ አለመሆኑን በቃላት ወይም በድርጊት መግለጽ ይገባዋል። ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች፣ ራሱን መርዳት የማይችል ሰው፣ ሕክምና ላይ ያሉ፣ በሥራ ምክንያት በበዳዩ ጥገኝነት ያሉ ግለሰቦች ግን አለመስማማታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲያቀርቡ አይገደዱም።

**ወሲባዊ ትንኰሳ ወይም ሴራ ሲከሰት መቼ ነው አቤቱታ ማቅረብ የሚያስፈልገው?**
ወሲባዊ ትንኰሳ ወይም የሴራው ድርጊት በሚከሰትበት ጊዜ አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል። አቤቱታውን ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ **እስከ** 3 ዓመት ባለው ጊዜ ማቅረብ ይቻላል። ለተፈጸመው ድርጊት በተቻለ መጠን ተጨባጭ ማስረጃ ማዘጋጀትና እንዲሁም በምስክሮች ማጠናከር (ማለትም ለጓደኛ//ቤተሰብ መናገር) ይመረጣል።

**በትንኰሳው ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች፡** ሕጉ 4 አማራጮችን ያቀርባል። ሁሉንም አማራጮች ወይም ከፊል አማራጮችን መጠቀም እንደዚሁም እነዚህን አማራጮች ጐን ለጐን መጠቀም ወይም አንዱን ከሌላ በኋላ መጠቀም ይቻላል።

- ውስጣዊ የዲሲፒሊን ፍርድ – በደረሰው ወሲባዊ ትንኰሳ ላይ ወደ አሠሪ/በሥራው ቦታ የወሲባዊ ትንኰሳ ተቆጣጣሪ ወደሆነው በመቅረብ
- አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል። ይህም ውስጣዊ የዲሲፒሊን ሂደቶችን ለማስጀመር ነው።
  በሠራተኞች ጉዳይ ፍርድ ቤት – ወሲባዊ ትንኰሳ የፈጸመውን፣ ሴራ የጠነሰሰውን እና አሠሪውን/አሠሪዋን መክሰስ እንዲሁም የገንዘብ ካሣ ለመቀበል ክስ መመሥረት ይቻላል።
- በሲቪል ፍርድ ቤት – ወሲባዊ ትንኰሳ የፈጸመው የገንዘብ ካሣ እንዲከፍል ክስ ማቅረብ ይቻላል። ከፍተኛው የቅጣት መጠን 50 ሺህ ሼቄል ነው።
- ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ አቤቱታ ማቅረብ – ይህ የሚደረገው የወንጀል ክስ ሂደት ለመጀመር ተብሎ ነው።

**የአሠሪው ግዴታዎች** – የሰው ኃይል ኩባንያ ኃላፊነት ከተራ አሠሪ ኃላፊነት ጋር እኩል ነው። አሠሪው በሥራው ቦታ ወሲባዊ ትንኰሳ እንዳይፈጸም አስፈላጊዎቹን እርምጃዎች መውሰድ አለበት። አሠሪው ወሲባዊ ትንኰሳ ወይም ወሲባዊ ሴራ በሥራው ቦታ እንዳይከሰት እርምጃዎችን ያልወሰደ ከሆነ ሠራተኞቹ በፈጸሙት ወንጀል ሊከሰስ ይችላል። አሠሪው ማድረግ ያለበት የሚከተሉትን ነገሮች ነው።

- አሠሪው ወሲባዊ ትንኰሳን በሚመለከቱ ጉዳዮች በሥራው ቦታ ኃላፊ መመደብ
- አሠሪው ወሲባዊ ትንኰሳ ወይም ሴራ የተፈጸመበት ሰው አቤቱታውን እንዴት በተቀላጠፈ መንገድ ማቅረብ እንደሚችል መወሰን
- አሠሪው በእሱ ሥር ያሉት ሠራተኞች በሙሉ በሥራ ባልደረቦቻቸው ሆነ በመሥሪያ ቤቱ ደንበኞች ላይ ወሲባዊ ትንኰሳ ወይም ሴራ እንዳይፈጽሙ መንገርና ማስጠንቀቅ
- አሠሪው ወሲባዊ ትንኰሳ በተመለከተ ለሠራተኞቹ ገለጻና መመሪያ መስጠት እንደዚሁም እያንዳንዱ ሠራተኛ በነዚህ ዓይነት እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፍ ማስገደድ
- ከ25 ሠራተኞች በላይ የሚያስተዳድር አሠሪ ወሲባዊ ትንኰሳን የሚመለከቱ መመሪያዎችንና ደንቦችን ለሠራተኞቹ ጐላ ተብሎ በሚታይ ቦታ ላይ መለጠፍ/ማስቀመጥ

**አሠሪው አቤቱታዎችን በማጣራት የሚያደርጋቸው፡** አሠሪው የኃላፊውን ማጠቃለያዎችና አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ከ7 የሥራ ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ከታች ከተዘረዘሩት ውስጥ አንድ እርምጃ እንዲወስድ ያስፈልጋል

- ሥራው የማይስተጓጐል ከሆነ "ወሲባዊ ተንኳሽ የተባለውን" ከተበዳዩ አካባቢ ማራቅ
- ድርጊቱ ተመልሶ እንዳይፈጸምና አቤቱታ ላቀረበው ሰው የደረሰበትን ጉዳት ለመቀነስ እርምጃ መውሰድ
- በሥራው ቦታ ባለው የሥነ ሥርዓት መመሪያዎች መሠረት ዲሲፒሊናዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ሂደት መጀመር

አሠሪው የሰጠውን ውሳኔዎች በተመለከተ ለአቤቱታ አቅራቢው፣ "ወሲባዊ ተንኳሽ ለተባለው" እና ለወሲባዊ ትንኮሳ ተቆጣጣሪ/ኃላፊ በጽሑፍ መስጠት ይኖርበታል።

## ለማን ማመልከት እንደሚቻል

**በኢንዱስትሪ፣**
- የሥራ ቦታ እኩልነት አስፈጻሚ ኮሚሽን
  02-6662780
  shivion@moital.gov.il

**የወሲብ ጥቃት ለደረሰባቸው እርዳታ የሚሰጡ ማዕከሎች ኅብረት፡**
ስልክ ቁጥር 1202

**በስልክ ምክርና መመሪያ የሚሰጡ የሴቶች ድርጅቶች፡**
- ኤሙና ስ.ቁ. 03-6857179
- ቪጾ ስ. ቁ. 03-6923825
- ናዓማት ስ. ቁ. 03-5254422
- በእስራኤል የሴቶች መብት ተሟጋቾች ስ. ቁ. 03-6123990

በሥራ ቦታ የወሲባዊ ትንኰሳ ተቆጣጣሪ/ኃላፊ፡

ድርጅት/ኩባንያ ____________

የተቆጣጣሪው/ዋ ስም ____________

የስልክ ቁጥር ____________

**ወሲባዊ ትንኰሳን የመከላከል ግዴታ ዓላማ የሰው ልጅ ክብርና ነጻነትን ለማስከበር እንዲሁም በጾታዎች መካከል ያለው እኩልነት እንዲስፋፋ ለማድረግ ነው።**

לפני